በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከማርች 21-31 እና ከኤፕሪል 1-10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ** - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 4 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2024 የሚኖረዉየቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 8 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 9 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -

እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት ቀናቶች በመካከለኛው፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በሃዋሳ 3.5፣ 2.1 እና 3.7፤ በበህር ዳር 4.3፣ 2.4 እና 6.3፤ በኮምቦልቻ 7.0፤ በደብረ ማርቆስ 10.0 እና 7.2፤ በጎንደር 7.1 እና 8.2፤ በጎሬ 1.0 እና 3.0፤ በጅማ 1.4፤ በነቀምቴ 5.6፣19.0 እና 1.8፤ በአዲግራት 11.3 እና 3.6፤ በአይራ 3.2፣1.5 እና 10.5፤ በአለም ከተማ 9.2፤ በአሊያ 3.0፤ በአማን 2.3 እና 32.5፤ በአምባ ማሪያም 9.4፣ 23.4፣ 1.6 እና 2.6፤ በአምደ ወርቅ 3.7፣ 2.9 እና 6.4 በአንገር ጉቲን 2.4፣ 5.0፣ 2.4፣ 8.0፣ 2.0 እና 3.4፤ በአርጆ 14.8፤ በአሶሳ 3.4 እና 14.5፤ በአፅቢ 2.5፤ በአዋሽ አርባ 3.0፤ በአየሁ 4.2 እና 1.2፤ በአይከል 2.6፤ በባቲ 14.5፤ በበደሌ 3.8 እና 70.7፤ በብላቴ 6.3፣3.8 እና 3.6፤ በቡሬ 6.7፣ 39.3 እና 6.0፤ በቡርጂ 15.6 እና 10.7፤ በቻግኒ 2.4 እና 7.5፤ በጨፋ 2.7 እና 4.5፤ በጭራ 12.4፣ 9.4፣ 1.5 እና 26.0፤ በዳንግላ 4.0፣ በደባርቅ 1.5 እና 1.2፤ በደብረ ታቦር 1.4 እና 6.2፤ በደብረ ወርቅ 7.2፤ በደምቢ ዶሎ 29.5፣17.5 እና 4.0፤ በኢጃጂ 6.2 እና 2.2፤ በፍቼ 4.0 እና 5.6፤ በፉኚዶ 1.0 እና 1.9፤ በጋምቤላ 2.8 እና 5.2፤ በጋቲራ 10.8 እና 17.8፤ በጊዳ አያና 3.0 እና 1.4፤ በጊምቢ 1.9፣ 1.1፣ 5.4 እና 2.1፤ በጉንዶ መስቀል 1.6፣ 4.0፣ 4.5 እና 4.0፤ በሆሳና 1.3፤ በእምድብር 7.0፤ በካቺሴ 3.3፣ 1.3 እና 5.5፤ በላሊበላ 15.4 እና 1.0፤ በላሬ 6.2 እና 12.0፤ በሊሙገነት 15.5፣ 6.8 እና 9.6፤ በማይጨዉ 31.5 እና 13.8፤ በማጀቴ 6.3፤ በማሻ 70.6 እና 1.4፤ በመካነ ሰላም 18.4፣ 5.6፣ 13.0፣ 5.5 እና 23.6፤ በሞጣ 3.5፣1.5 እና 22.2፤ በንፋስ መዉጫ 4.4፣ 7.3፣ 10.9 እና 15.7፤ በነጆ 3.5፣ 4.0፣ 5.9 እና 5.2፤ በሳዉላ 7.5 እና 7፤ በሶኮሩ 2.5፣ 4.2 እና 4.4፤ በስንቃጣ 12.0፤ በሻዉራ 2.2፤ በሸርቆሌ 7.0፤ በሲርንቃ 5.2፤ በቴፒ 7.1፣ 1.4 እና 25.6፤ በተርጫ 1.0፤ በፅፅቃ 1.8 እና 1.0፤ በወገልጤና 1.8 እና 1.6፤ በወላይታ ሶዶ 3.2 እና 6.0 እንዲሁም በየትኖራ 6.7፣1.1 እና 2.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣4፣3 እና 5፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋግህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ ንዌር፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ የየም ልዩ ዞን፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ ዞን ላይ ከ55-75 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር፣ቄለም ወለጋ እና ጅማ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ኮንታ እና ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ከጋምቤላ ክልል ንዌር፣ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊ፣ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ፤ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ማዕከላዊ፣ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2 እና 4 ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ አካባቢዎች የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ30-40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ እንደተመዘገበ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ይጠቁማሉ(ምስል 1)። ባለፉት አስር ቀናት ከ40 ዲ.ሴ በላይ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በጎዴ፣ በአቦቦ፣ በኤሊ.ያና በፉኝዶ ሲሆኑ፤ በጎዴ፣ በጋምቤላ እንዲሁም በላሬና በመተማ ከሌሎቹ ቆላማ አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር በመጠኑ ከፍተኛ ሲሆን፤ ለተከታታይ ቀናት ከ40 ዲ.ሴ፤ እንዲሁም በጋምቤላ 43.8 ዲ.ሴ የሚደርስ የሙቀት መጠን ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፣ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች እርጥበታማ ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ አዎንታዊ ሚና ነበረው በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በላይኛውና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ በላይኛው ምስራቃዊ እና በጥቂት የታችኛው አባይ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄደው ከማርች አጋማሽ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በማርች ሶስተኛው አሥር ቀናት አብዛኛዎቹን የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ ቦታዎችን ያካተተ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይስተዋልባቸዋል፡፡


በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ እና የሰሜን ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ እንዲሁም የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ፣ የመካከለኛዉ፣ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የፋፈን፤ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚያዳርስ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

(ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ የሊበን፣ የአፍዴር፣ የኤረር እና የነጎብ ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል በጋምቤላ፣ ቋራ፣ መተማ፣ መተራ፣ ዱብቲ፣ ሎጊያ፣ አብዓላ፣ አፍዴራ፣ ጎዴ፣ ቀብሪ ደሃር፣ ደጋሀቡር፣ ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በመጪዎቹ የኤፕሪል አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ።

Rainfall performance (mm) for 1-10 Apr 2024




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10፣ 2024 የሚኖረው
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በርካታ ቦታዎችን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ እርሻ ሥራን፣ ለአፈር እርጥበት መሻሻል ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከነውን ከፍተና ጠቀሜታ አለው፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## ኢ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ. ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛው የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ የላይኛው ተከዜ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ አዋሽ እና አፋር ደናክል ተፋሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን፤ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውሃ ሀብትን ከማሻሻል አኳያ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et